**ኀዲጎ ተሰዓ**

ኀዲጎ ተሰዓ ወተስዓተ ነገደ

ማዕከለ ባሕር/2/ ቆመ ማዕከለ ባሕር

ጌታችን ተጠምቆ በዮሐንስ እጅ

የኃጢያት ደብዳቤ ቀደደ በአዋጅ

ባሕረ ዮርዳኖስ መቆም ተስኗት

ሸሸች ወደ ኋላ ከመለኮት ፊት

አዝ . . . . . .

  ቀላያት ዘለሉ ዕፅዋት ዘመሩ

  አንደበት አገኙ ግዑዛን አወሩ

  የልጁን ጌትነት ክብሩን ሊያስረዳ

  በደመና መጣ አብም ተሰናዳ

አዝ . . . . . .

  ከወደላይ መጣ ምስጢር ያለው ቃል

  የምወደው ልጄን እርሱን ስሙት ሲል

  አደለን ዳግመኛ ሁለተኛ ልደት

  ከጐኑ በወጣው በማየት ሕይወት ጥምቀት

አዝ . . . . . .

  ዘጠና ዘጠኙን መላእክትን ትቶ

  በዮርዳኖስ ቆመ አምላክ በአትሕቶ

  ማድነቅ ይገባናል የውኃን ሥርዓት

  በዓሉ ዛሬ ነው ቃና እና ጥምቀት